ገ ጽ


የቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ አሞላል መመሪያ ............ 78

ክፍል 1 የአካባቢ መለያ ............ 79

ዓምድ 1–3 ክፍለ ሀገር፣ አውራጃ፣ ወረዳ ............ 79
ዓምድ 4–5 ከተማና ከፍተኛ ............ 79
ዓምድ 6 የመቆጣጠሪያ ቦታ ............ 79
ዓምድ 7 ቀበሌ ማኅበር ............ 79
ዓምድ 8 የቆጠራ ቦታ ............ 79

ክፍል 2 መሠረታዊ የሕዝብ ባሕሪያት ማጠቃለያ ............ 80

ዓምድ 9 የቤት ተራ ቁጥር ............ 80
ዓምድ 10 የነዋሪ ዓይነት ............ 80
ዓምድ 11 የነዋሪ ዓይነት ተራ ቁጥር ............ 80
ዓምድ 12 ስም ............ 80
ዓምድ 13 የሰዎች ብዛት ............ 81
ዓምድ 14–15 ባለፉት 12 ወራት የተወለዱ ልጆች ብዛት የሞቱ
አባላት ብዛት ............ 81
ዓምድ 16 ማንበብና መጻፍ የማይችሉ የሚችሉ ............ 81
ዓምድ 17 ብሔረሰብ ............ 82
ድምር ............ 82
ጠቅላላ ድምር ............ 82
ዓምድ 18 ጠቅላላ የቤተሰብ ብዛት ............ 83
ዓምድ 19 ጠቅላላ የመኖሪያ ቤቶችና ለመኖሪያና ለድርጅት
የሚያገለግሉ ቤቶች ብዛት ............ 83
ዓምድ 20 የቆጣሪዎችና የተቆጣጣሪዎች ስም፣ ፊርማና ቀን ... 83

ስለ ቆጠራ ቦታ ካርታ ዝርዝር መግለጫ ............ 84

የቆጠራ ቦታ ካርታ አጠቃቀም ............ 85

ዕዝል 1 ............ 94

# የ1976 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕዝብና ቤቶች ቆጠራ

## የቆጣሪዎች መመሪያ — ለከተማ

### 1. መግቢያ

የአንድን አገር ሕዝብ ብዛት፣ የሕዝቡን የቦሻልና የኢኮኖሚ ሁኔታ በትክክል የሚያመለከት መረጃ ከሌለ አስተማማኝ ዕቅድ ለማዘጋጀትና ፖሊሲ ለማውጣት አዳጋች ይሆናል፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ ከተማውንና ገጠሩን በሚመለከት ዕቅዶች በሚዘጋጁበት ጊዜ ውሱን የሆኑ የሕዝብና የቤቶች መረጃዎች ሊገኙ የቻሉት አልፎ አልፎ ከናሙና ጥናቶች ከተሰበሰቡት መረጃዎች ሲሆን እነዚህ መረጃዎች አስተማማኝ ካለመሆናቸውም በላይ በጣም የቆዩ ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የተሟላ፣ በሩ ያለ፣ ወቅታዊና አስተማማኝ የሆነ የአስታቲስቲክስ መረጃ በገጠሩና በከተማው የሚደረገው ለኢኮኖሚና ለቦሻል ዕቅድ እንቅስቃሴ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንን በመገንዘብና ሁኔታዎችን ለማመቻቸት በግንቦት ወር 1976 ዓ.ም. ጠቅላላ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ይካሄዳል፡፡

### 2. የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ትርጉም

የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በተወሰነ ወቅትና የአስተዳደር ክልል ስለ ሕዝብ ባሕሪያት፣ ስለማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እንዲሁም ስለቤቶች ሁኔታ የሚገልጹ አስታቲስቲካዊ መረጃዎች የመሰብሰብን፣ የማጠናቀርንና የመተንተንን ከዚያም አስተማማኝነቱንና ትክክለኛነቱን በመገምገም የተገኘውን ውጤት የማሰራጨትን ተግባራት ያጠቃልላል፡፡ ከዚህ ለመረዳት የሚቻለው ቆጠራው በሕዝብ ወይም በቤቶች ብዛት ላይ ብቻ ባያተኩር ስራትና ጥልቀት ኖሮት የተለያዩ የማሕበራዊና የኢኮኖሚያዊ መስኮች የሚሸፍን ስለ መሆኑ ነው፡፡ ቆጠራው የሚካሄድበት ክልል በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የአንድን አገር የአስተዳደር ክፍሎች ሊያጠቃልል ስለሚችልም በቆጠራው ለተሸፈኑት ከዝቅተኛው የአስተዳደር ክፍል ጀምሮ የተለያዩ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ነክ መረጃዎች ለማቅረብ ያስችላል፡፡

ሰ. በቤት ሳልተገኙ ቤተሰቦች በቤቱ ለሚጠየቁት ምላሽ የሚሰጥ አዋቂ አባል ባለ መገኘት መጠይቁ ሳልተሞላላቸው ቤተሰቦች ተደጋጋሚ ጉብኝት ለማድረግ ተደጋጋሚ ጉብኝት የሚካሄድባቸው የቤተሰብ ኃላፊዎች መመዝገቢያ ቅጽ መሙላት፣

ሸ. በየአለቱ የተሞላውን መጠይቅ በመመርመር፣ መሞላት ሲገባቸው ያልተሞሉ ዓምዶች፣ ሊገናዘቡና ሊመባከሩ ያልቻሉ ዓምዶችና ባይቆጠሩ የተዘለሉ ቤተሰቦች ካሉ ወዲያውኑ ወደ ቤተሰቡ በመሄድ አስፈላጊውን እርማት ማድረግ፣

ቀ. ቆጠራው እንደተጠናቀቀ ለቆጠራው ቦታ የማጠቃለያ ቅጽ መሙላት፣

በ. ቆጠራው በትክክልና በተሟላ ሁኔታ መጠናቀቁን ተቆጣጣሪው ካረጋገጠ በኋላ አስፈላጊ ዶኩሜንቶችና ዕቃዎች ለተቆጣጣሪው ማስረከብ፣

6. <u>ቆጠራውን ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ዶኩሜንቶችና ሌሎች ዕቃዎች ዓይነት ዝርዝር</u>

ሀ. የቆጠራ ቦታ ካርታና የቆጠራ ቦታ ዝርዝር መግለጫ፣

ለ. የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅት መመዝገቢያ ቅጽ፣ /ቅጽ 1/

ሐ. የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ጥራዞች፣

መ. የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የቆጣሪዎች መምሪያ፣

ሠ. የተደጋጋሚ ጉብኝት የሚካሄድባቸው የቤተሰብ ኃላፊዎች መመዝገቢያ ቅጽ፣ /ቅጽ 2/

ረ. የቆጣሪ እለታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት መመዝገቢያ ቅጽ፣ /ቅጽ 3/

ሰ. ለቆጠራው ቦታ የሚሞላ ማጠቃለያ ቅጽ፣ /ቅጽ 4/

ሸ. የቆጣሪ ቦርሳ፣ እርሳስ፣ ላፒስ፣... ወዘተ

ቀ. የመታወቂያ ወረቀት፣ ባጅ.... ወዘተ

7. <u>የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ የመረጃ አሰባሰብና አፈጻጸም ቅደም ተከተል</u>

በቆጠራ ክልል ውስጥ የሚገኙ ማንኛውም ቤቶችና ነዋሪ ቤተሰቦች በእያንዳንዱ ቤተሰብ የሚኖሩ መደበኛ የቤተሰብ አባላት በሙሉ በቆጠራው ይሸፈናሉ። ቆጠራው የሚከናወነው ቆጣሪው ከቤት ወደ ቤት በመሄድ ተፈላጊውን መረጃ ጠይቆ በመመዝገብ ይሆናል።

እንደሚታወቀው የገጠሩ በገበሬ ማኅበራት ከተማው ደግሞ በከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት የተደራጀ ነው:: ለሕዝብና የቤቶች ቆጠራ እንዲሁም ወደፊት ለሚከናወኑ የሶሻልና የኢኮኖሚ ጥናቶች ለማካሄድ እንዲያመች እያንዳንዱ የከተማ ነዋሪዎች ማኅበር ክልልና የገበሬ ማኅበር ክልል በተወሰኑ የቆጠራ ቦታዎች ተሸንሽኖ የቆጠራ ቦታ የሚያሳይ ካርታ ተዘጋጅቷል:: እያንዳንዱ "የቆጠራ ቦታ" ከ150 — 200 የሚደርሱ ቤተሰቦች በውስጡ ሲኖሩት እንደዚሁም ከ5 — 6 የቆጠራ ቦታዎች አንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ ተዘጋጅቷል::

አንድ ቆጣሪ በተመደበለት የቆጠራ ቦታ ውስጥ ብቻ ቆጠራውን ያከናውናል:: ስለዚህ እያንዳንዱ ቆጣሪ የተመደበበትን የቆጠራ ቦታ ወሰን በቅድሚያ ማወቅ ስለለበት የቆጠራ ቦታ ካርታ ይሰጠዋል:: በዚህ መሠረት ቆጠራ ከመጀመሩ በፊት በካርታው አማካኝነት የቆጠራውን ቦታ ወሰን በመርገጥ ከልሉን ይለያል:: ከዚያም በቆጠራ ቦታ ውስጥ የሚገኙትን ቤቶች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶች በሙሉ ሥርዓት ባለው መንገድ ይመዘገባል:: በቆጠራው ጊዜ ቤተሰቦችና ቤቶች ሳይቆጠሩ እንዳይታለፉ ወይም በመደጋገም እንዳይቆጠሩ እንደዚሁም ከተመደበለት የቆጠራ ቦታ ውጭ በመውጣት ቆጠራ እንዳያካሄድ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: በቆጠራው ቦታ ውስጥ የሚገኙት የቤተሰቦችና የቤቶች ምዝገባ ከተጠናቀቀ በኋላ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ መጠይቆች ይሞላሉ::

በተቻለ መጠን መረጃው በሚሰበሰብበት ጊዜ መረጃ ሰጪው የቤተሰቡ ኃላፊ እንዲሆን ቢመረጥም የቤተሰብ አባላትን ዝርዝር ሁኔታዎች በሚመለከት በሚሞላበት ጊዜ ከየአባላቱ በቀጥታ ቢሰበሰብ ይሻላል::

አንዳንድ ጊዜ የአንዱን ቤተሰብ መረጃ በመጀመሪያ ጉብኝት ጊዜ ማግኘት አይቻልም ይሆናል:: በዚህ ጊዜ ከሦስት ጊዜ የማይበልጥ ተደጋጋሚ ጉብኝት በማድረግ መረጃዎቹ እንዲሰበሰቡ ይሆናል:: ከሦስተኛ ጉብኝት በኋላ ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ካልተቻለ ሁኔታውን ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ ማሳወቅ ይኖርበታል::

እነዚህ ዞኖች /ብሎኮች/ አብዛኛውን ጊዜ ሥርዓት ባለው ሁኔታ በመንገድ እንደ ሚከፈሉ ይገመታል። ከዚህም በላይ በከተሞች ቤቶች የቀበሌ መለያ ቁጥር ተሰጥቶአቸዋል። የከተማ የቆጠራ ቦታ የሚያሳይ ምሳሌ ከዚህ ቀጥሎ ተመልክቶአል። ምዝገባው በሚካሄድበት ወቅት የሚከተሉት ተግባራት መፈጸም አለባቸው።

ሀ/ በመጀመሪያ የቆጠራ ቦታን ድንበር ዞር ማየትና ማጥናት፤

ለ/ የቆጠራ ቦታን በዞኖች /በብሎኮች/ መሸንሸን፤

ሐ/ ለተሸነሸኑት ዞኖች /ብሎኮች/ በቆጠራ ቦታው ካርታ ላይ ቁጥር መስጠት፤

መ/ በቆጠራው ቦታ በሰሜን ምዕራብ ከሚገኘው ዞን /ብሎክ/ በመጀመር ወደ ምሥራቅ በመጓዝ እያንዳንዱ ቤት፣ ቤተሰብና ድርጅት በቅደም ተከተል መመዝገብ፤

ሠ/ ምዝገባው የሚከናወነው በእያንዳንዱ ብሎክ የሚገኙትን ቤቶች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶች መዝግቦ ከጨረሱ በኋላ ወደሚቀጥለው ብሎክ በመሸጋገር ይሆናል፤

ረ/ ምዝገባው የተጀመረበትን ቦታ ለማመልከት በቆጠራው ካርታ ከመነሻው ላይ የ"x" ምልክት ማድረግ ያስፈልጋል። ዋናው ቆጠራው በሚካሄድበትም ጊዜ በካርታው ላይ የ"x" ምልክት ከተደረገበት ቦታ መጀመር ያስፈልጋል፤

ሰ/ ምዝገባው በሚካሄድበት ጊዜ የመኪና መንገድን ብቻ መከተል ሳይሆን ወደ ቤትና ግቢ በስተጀርባ የሚያስኬዱትን የእግር መንገዶች በመጓዝ ሰዋራ ቤቶችን በሙሉ መመዝገብ ያስፈልጋል፤

ሸ/ የምዝገባው ሥራ ተጠናቀቀ የሚባለው በቆጠራ ቦታው ውስጥ የሚገኙት ቤቶች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶች በሙሉ ሲመዘገቡ ነው።

በገጠር የምዝገባው ሥራ አስቸጋሪ ስለማይሆን በከተማ ቆጠራ ቦታ የምዝገባ አፈጻጸም ሥርዓት በገጸ 10 በተሰጠው ምሳሌ እንደተመለከተው ይሆናል።

1ኛ/ ክፍል አንድ ዓምድ 13 የቤተሰብ ተራ ቁጥር አይሞላም፡፡

2ኛ/ ክፍል አራት ስለ መኖሪያ ቤቶች ዝርዝር መረጃ አይሞላም፡፡

ነገር ግን በዓምድ 17 "ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና" በሚመለከት ለአያንዳንዱ የጋር ዱሽ መኖሪያ ቤት ነዋሪ ከሚከተሉት አንዱን በመምረጥ ሸኛ ኮዱ ይሞላል፡፡

0 = አዳሪ ተማሪ
1 = አዳሪ ሠልጣኝ
2 = ተኝቶ ታካሚ
3 = እስረኛ
4 = ከንትራት ሠራተኞች
5 = የጦር ኃይሎች አባል
6 = የሆቴል እንግዳ
7 = የሆቴልና የሆስቴል ነዋሪ
8 = ሌላ /ይገለጽ/

ለ. ቤት የሌላቸው ነዋሪዎችን በሚመለከት

በዓምድ 9 የነዋሪ ዓይነት በሚመለከት ቤት የሌላቸው ለሚለው መልስ ኮድ ከበ በማድረግ ኮዱ በተሰጠው ካርድ ኮለም 23 ውስጥ ለተሞላላቸው የሚከተሉት ዓምዶች ወይም ክፍሎች አይሞላላቸውም፡፡

1ኛ/ ክፍል አንድ የቤት ተራ ቁጥር፣ የቤት ቁጥር፣ የቤት ንዑስ ቁጥርና የቤተሰብ ተራ ቁጥር መኖሪያ ቤት ለሌላቸው ነዋሪዎች ከ10–13 ያሉት ዓምዶች አይሞሉም፡፡

2ኛ/ በክፍል ሁለት ዓምድ 17 "ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና" በሚለው ምንም አይሞላም፡፡

3ኛ/ ክፍል ሦስት "ስለሞት መረጃ" አይሰበሰብም፡፡

4ኛ/ ክፍል አራት "ስለ መኖሪያ ቤቶች ዝርዝር መረጃ" አይሞላም፡፡

ይህ መጠይቅ በቆጠራው ቦታ የቤት የቤተሰብና የድርጅት መዝገብ ከተጠናቀቀ በኋላ ቆጠራው ከቤት ቤት በመሄድ ስለ ቤተሰብ አባላትና ቤቶች በሕሪያት በሚመለከት ዝርዝር መረጃ የሚሰበሰብበት ነው፡፡ ለክፍለ ሀገር፣ ለአውራጃ፣ ለወረዳ፣ ለከፍተኛ፣ ለመቆጣጠሪያ ቦታ፣ ለቀበሌ ማኅበር፣ ለቆጠራ ቦታ የሚሞላው ኮድ በሕዝብ ቆጠራው ካርታ በቆጠራ ቦታ ማኅደር ለእነዚህ ክፍሎች የተሰጡትን ኮዶች በመጠይቆች ጥራዝ ሽፋን ላይ በተገበው ዓምዶችና ካርድ ኮለሞች ላይ ይሰበጣሉ፡፡

<u>ኮድ</u> <u>ብሔረሰብ</u>

37.... የምባ፣ የማ፣ ዳንጀር
38.... ቤንቾ፣ ቤንችኛን፣ ቤ፣ ጊሚራ
39.... ከፋ፣ ከፋቾ /ጎንጋ፣ ቦሻጋር/
40.... ናኦ፣ ናዎ
41.... ሞቻ፣ ሼኪ
42.... ሻኮ፣ ጊዙ፣ ቡሳ፣ ደርባ፣ ደርቦ፣ ደርቦ
43.... ሽናሻ፣ ቦር /ጓርቻ፣ ችክ፣ ቦሜን ችክ/
44.... ደሜቴ፣ ኩሎ፣ ዳውሮ
45.... ኮንታ
46.... ባስኬቶ፣ አንጺሳ፣ ማሼራ /ዶኮ፣ ዶሎ ዶሳ/
47.... ዶርዜ
48.... ጋሞ
49.... ጋንጁሌ፣ ባጫ
50.... ጎፋ፣ ገኑ
51.... ቁጫም፣ ቋጫም፣ ጋጻም፣ ሀሩር
52.... ኮይራ፣ አማር፣ አመርቴ፣ ጊዲቾ
53.... ማሌ
54.... ማሎ፣ ዳውሳ
55.... ጨራ
56.... ወሳይታ
57.... ዘይሴ፣ ዘርጉሳ
58.... አይዳ
59.... ሱርማ፣ ቲርማ፣ ዳማ
60.... ጉጉ፣ ቢጉ፣ ሙጉጂ፣ ዩጂ፣ ኘይኒ
61.... መኤን፣ መቀን፣ ዳይና፣ ባርከሞ /ቦዲ፣ ቦዲ፣ ተሻና፣ ሚኒት/
62.... መበንጎ፣ ማጃንግ፣ መዠንገር
63.... ሙርሲ፣ ሙን፣ ሙኒ፣ ኘካሰበንግ፣ ጣማ
64.... ቡሬ፣ ቻይ፣ ኘከርማ
65.... ዘልማም፣ በሌ፣ ማሌ፣ ዳልማም
66.... ሙርሌ /አሰም ሙርሌ፣ ኦም ሙርሌ፣ ሌሎች/
67.... አኙዋ፣ አኙዋክ፣ የምቦ
68.... ማበን

ኮድ ብሔረሰብ

69.... ትግሬ፣ አበጋር
70.... ኛንጋቶም፣ ቶርካና፣ ቡና
71.... በርታ
72.... ጋሚሊ
73.... ጎበት
74.... ሚቁ
75.... ኒዓሺ
76.... ፈኩንኩም
77.... ሎንዳ
78.... ገበቶ
79.... ቤኒሻንጉል
80.... ጀበሳዊ፣ አርቦ
81.... ኩናማ፣ በዓ፣ ካዛን፣ በዛ ሎማይሸ በርካ፣ ቢታማ፣ ኢሉት፣ ማርዓ፣ በቲት፣ በጎዓስ፣ ቲካ/
82.... ወይጠ
83.... ፈሳሽ፣ ካይሳ፣ ቤተስራኤል
84.... ኮማ፣ ኮሞ፣ ሀያሀያ፣ መደን
85.... ጉሙዝ፣ ጋንዛ፣ ጋንዛ ሊስ፣ ሸይ ኡኩሁ፣ ገበጠ/
86.... ከቀማ፣ ቢማ
87.... ሸታ፣ ቺታ፣ ሳንጋ
88.... ናራ፣ በሪያ፣ ማርዓ /ሂገር፣ ሞጋሪብ ሳንቶራ፣ ኮይታ፣ ኮይቻ/
95.... ብሔረሰባቸው ያልታወቀ ኢትዮጵያውያኖች
96.... ዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የውጭ ሰዎች
97.... ከተሸያዩ ብሔረሰቦች የተወለዱ
98.... ሌሎች ብሔረሰቦች

<u>ዓምድ 23 — 26 ፡ የትውልድ ቦታ</u>

የአንድ ግለሰብ የትውልድ ቦታ ግለሰቡ በተወለደበት ጊዜ እናቱ ትኖርበት የነበረው መደበኛ የመኖሪያ ቦታ ሲሆን በከተማ ትኖር ከነበረ ትኖርበት የነበረ ከተማ፣ ገጠር ትኖር ከነበር ደግሞ ትኖርበት የነበረ ወረዳ ነው፡፡ የትውልድ ቦታ በሚመዘገብበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው በሆስፒታል ወይንም በሌላ ክፍለ ሀገር፣ አውራጃ ወይም ከተማ ወይም በእናቱ ወላጆች መኖሪያ ቢወለድ የግለሰቡ የትውልድ ቦታ ግለሰቡ በተወለደበት ጊዜ እናት የቋ ትኖርበት የነበረ መደበኛ መኖሪያ ይሆናል እንጂ ግለሰቡ የተወለደበት ሆስፒ ታል የሚገኝበት ከተማ፣ ወረዳ፣ አውራጃ ወይም ክፍለ ሀገር አይሆንም፡፡ ነገር ግን እናቱ ልጅ ከተወለደ በኋላ በተወለደበት ቦታ ማለት በሆስፒታል፣ በእናቱ ወላጆች መኖሪያ፣.... ወዘተ ከስድስት ወር በላይ ከቆዩ የሕፃኑ የትውልድ ቦታ ሆስፒታሉ የሚገኝበት ከተማ ወይም የልጅ እናት ወላጆች የሚኖሩበት ከተማ ወይም ወረዳ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል የትውልድ ቦታ በሚከተለው መሠረት በዓምዱ በተሰጠው ቦታ ይሞላል፡፡

የትውልድ ቦታ የሚለው ጥያቄ አራት ዓምዶችን የያዘ ሲሆን እነርሱም፣

ዓምድ 23 — ከተማ

ዓምድ 24 — ወረዳ

ዓምድ 25 — አውራጃ

ዓምድ 26 — ክፍለ ሀገር

1. የአንድ የቤተሰብ አባል የትውልድ ቦታ ቆጠራ በሚካሄድበት ከተማ ከሆነ ግለሰቡ በዚሁ ከተማ የተወለደ መሆኑን ለመግለጽ ከ23—26 ባሉት ዓምዶች በተሰጡት ክፍት ቦታዎች "እዚሁ" የሚል ቃል ይመዘገብል፡፡ ከዚያም በካርድ ኮለም 42—49 ሥር ባሉት ሣጥኖች "××፣ ××፣ ××፣ ××" ይሞላል፡፡ ለምሳሌ የሕዝብ ቆጠራው የሚካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ ከሆነና የቤተሰቡ አባል አዲስ አበባ የተወለደ ከሆነ የዚህ ግለሰብ የትውልድ ቦታ እዚሁ ከተማ ስለሆነ ከ23—26 ባሉት ዓምዶች "እዚሁ" የሚል ቃል ተመዝግቦ 42—49 ባሉት ኮርድ ኮለሞች ሥር የሚገኙት ሣጥኖች "××፣ ××፣ ××፣ ××" ይሞላሉ፡፡

በመሠረተ ትምህርት በሚሰጠው ትምህርት ማንበብና መጻፍ ችለው በሰሰ ቦታ ትምህርት ያልቀጠሉ የሁለተኛ ከፍሎትምህርት አንዳ ጠናቀቀ ይቆጠራሉ፣

03 = የ3ኛ ክፍል ትምህርት ሰጠናቀቀና ማንበብና መጻፍ ሰሚችሉ ሁሉ

04 = የ4ኛ ክፍል ትምህርት ሰጠናቀቀ ሁሉ

05 = የ5ኛ ክፍል ትምህርት ሰጠናቀቀ ሁሉ

06 = የ6ኛ " " " "

07 = የ7ኛ " " " "

08 = የ8ኛ " " " "

09 = የ9ኛ " " " "

10 = የ10ኛ ክፍል ትምህርት ሰጠናቀቀ ሁሉ

11 = የ11ኛ " " " "

12 = የ12ኛ " " " "

20 = ከ12ኛ ክፍል ትምህርት በሰይ የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ/ ሰማስገኘት በልታቀደ የትምህርት ፕሮግራም በሆነ ትምህርት ቤት፣ ተቋም ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ሰጠናቀቀ ሁሉ፡፡

21 = ከ12ኛ ክፍል ትምህርት በሰይ የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ. ኤስ. ሲ/ ያስገኛል ተብሎ በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም በኮሌጅ ወይም በዩኒቨርሲቲ የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ሰጠናቀቀ ግን ዲግሪ ሰሰገኙ ሁሉ፡፡

22 = የመጀመሪያ ዲግሪ /ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ፣ ኤል.ኤል.ቢ/ሳገኙና ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ሰሰቸው ሁሉ፡፡

23 = በዩኒቨርሲቲ በድሕረ ምረቃ ፕሮግራም /ከመጀመሪያ ዲግሪ በሰይ/ የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ሰጠናቀቀ ግን የኤም.ኤ፣ ኤም.ኤስ.ሲ ወይም ኤል.ኤል.ኤም ዲግሪ ሰሰገኙ ሁሉ፡፡

24 = የኤም.ኤ፣ የኤም.ኤስ.ሲ፣ ወይም የኤል.ኤል.ኤም /ማስተ የማስትሬት/ ዲግሪ ሰገኙ ሁሉ ወይም ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ሰሰቸው ሁሉ፡፡

25 = የዶክትሬት ዲግሪ ሰገኙ ሁሉ ወይም ተመሳሳይ ትምህርት ሰጠናቀቀ ሁሉ፡፡

26 = ማንበብና መጻፍ በሚገባ የሚችሉ ሆነው ግን ትምህርታቸው ወደ መደበኛ የትምህርት ደረጃ አመዳደብ ሊተረጐም ለማይችል ሁሉ፣ ለምሳሌ በገዳሞችና በሙስሊሞች የቄስ ትምህርት ቤቶች፣ በቁራን ትምህርት ቤቶች ብቻ ትምህርት ተከታትለው ማንበብና መጻፍ የቻሉ ቄሶች፣ ደብተራዎች፣ መነኩሳት፣ ሼኮች፣.... ወዘተ የጨረሱት የትምህርት ደረጃ እዚህ ይመደባል፡፡ እንደዚሁም በራሳቸው ጥረት የጎለመሶችን አርዓያ እየጠየቁ በመማርና አንደኛ ክፍል ከመጨረሳቸው በፊት ማንበብና መጻፍ በሚገባ የቻሉ ሁሉ የትምህርት ደረጃቸው እዚህ ይመደባል፡፡ መሠረተ ትምህርት እየተማሩ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ያጠቃልላል ።

ትምህርቱን ከመደበኛ ትምህርት ቤትና ዩኒቨርሲቲ ውጭ የተከታተለ ወይም በመከታተል ላይ ያለ ማንኛውም ሰው የጨረሰውን ከፍተኛ ክፍል ለማወቅ በተቋሙ የስንት ዓመት ትምህርት ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ደረጃ እንዳጠናቀቀ እና በመደበኛ ትምህርት ቤት የጨረሰውን ክፍል ወይም ደረጃ በማጣራት ሁለቱን በመደመር ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ከተወሰኑ ዓመታት በፊት ነርሶች ትምህርት ቤት ለመግባት ማጠናቀቅ የሚያስፈልገው በመደበኛ ትምህርት 8ኛ ክፍል ቢሆን በነርሶች ትምህርት ቤት የሚሰጠው የሙያ ትምህርት ሦስት ዓመት ቢፈጅ የጨረሱትን ከፍተኛ ክፍል ለማስላት 8 + 3 = 11 ይሆናል፡፡ ስለዚህ በካርድ ኮለሞች 55 እና 56 ውስጥ 11 ይሞላል ማለት ነው፡፡

ነገር ግን ወደ ነርስነት ትምህርት ቤት መግባት ይቻል የነበረው በመደበኛ ትምህርት ቤት የ11ኛን ክፍል ትምህርት በማጠናቀቅ ከሆነ ሁኔታው የተለየ ይሆናል፡፡ በዚህ የነርስነት ትምህርት ቤት ያለአንዳች መድገም የ3 ዓመት ትምህርት ያጠናቀቀና ሌላ ተጨማሪ መደበኛ ትምህርት ያልቀጠሉ ነርስ የጨረሰው ከፍተኛ ክፍል 14 /ማለት 11+3/ መሆን አለበት፡፡ በማታ ትምህርት ቤት፣ በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም፣ በንግድ፣ በተግባረ ዕድ፣ በቴሌኮሙኒኬሽን፣.....ወዘተ ትምህርት ቤቶች ወይም ተቋሞች ትምህርት የተከታተሉ ወይም በመከታተል ላይ ያሉ ሁሉ የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል በተመሳሳይ መንገድ መገኘት አለበት፡፡

እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስፈልገው በተለያዩ የትምህርት ተቋሞች የተማረ ገለሰብ የጨረሰው ክፍል ተብሎ የሚመዘገበው ከጨረሰው የትምህርት ደረጃ መሀከል ከፍተኛውን በመውሰድ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ነርስ በመደበኛ ትምህርት 11ኛ ክፍል አጠናቃ በነርሶች ተቋም ደግሞ የ3 ዓመት ትምህርት ብትጨርስ በተጨማሪም በማታ ትምህርት ቤት 12ኛ ክፍል ጨርሳ ትምህርቷን በመቀጠል በዩኒቨርሲቲ በማታ

ዓምድ 38 ሌሳ ቦታ የሚኖሩ

በጠቅላላው በሕይወት ከተወለዱ ልጆች መካከል ስንቱ ሌሳ ቦታ እንደሚኖሩ ጠይቆ በጽታ በመለየት በዓምድ 38 በካርድ ኮለሞች 70 እና 71 ይሞላል:: በሕይወት የወለዱዋቸው ልጆች ሌሳ ቦታ የማይኖሩ ከሆነ በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለሞች 70 እና 71 ውስጥ ኮድ "00" ይሞላል::

ዓምድ 39 የሞቱ

ከጠቅላላው በሕይወት ከተወለዱት ልጆች መካከል ስንቱ እንደሞቱ በመጠየቅ የሞቱትን ልጆች ብዛት በጾታ ለይቶ በዓምድ 39 በካርድ ኮለሞች 72 እና 73 ውስጥ ይሞላል:: በሕይወት ተወልደው የሞቱ ልጆች ከሌሉ ግን በዚህ ዓምድ በካርድ ኮለሞች 72 እና 73 ውስጥ ኮድ "00" ይሞላል:: ይህ ዓምድ በሚሞላበት ጊዜ ማስታወስ የሚያስፈልገው የሞቱት ልጆች ሲባል በሕይወት ተወልደው ነገር ግን ከተወለዱ በኋላ የሞቱትን መሆኑን ነው::

ዓምድ 40 ባለፉት 12 ወራት በሕይወት የወለዱዋቸው ልጆች ስንት ናቸው ?

ዕድሜአቸው አሥር ዓመትና በላይ የሆኑ ሴቶች ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በሕይወት የወለዱዋቸውን ሕፃናት ብዛት ጠይቆ በዓምድ 40 "ጠቅላላ" በሚለው ሥር በካርድ ኮለም 74 ብዛቱ ይመዘገባል:: እንዲሁም ባለፉት 12 ወራት በሕይወት ከተወለዱት እስከ ቆጠራው ዕለት ድረስ በሕይወት ያሉትን በዓምድ 40 "አሁን በሕይወት ያሉ" በሚለው ሥር በካርድ ኮለም 75 ውስጥ ይመዘገባል:: ባለፉት 12 ወራት ማለት ከቆጠራው ቀን በፊት የነበሩትን 12 ወራትን የሚያጠቃልል ይሆናል:: ለምሳሌ የቆጠራው ቀን ሚያዝያ 15 ቀን 1976 ዓ.ም. ቢሆን ከቆጠራው ቀን በፊት የነበሩት 12 ወራት የሚያጠቃልለው ከሚያዝያ 16 ቀን 1975 ዓ.ም. እስከ ሚያዝያ 14 ቀን 1976 ዓ.ም. ይሆናል ማለት ነው:: ሴትዮዋ ባለፉት 12 ወራት ልጅ ካልወለደች በካርድ ኮለም 74 እና 75 ኮድ "0" ይሞላል::

አበዛኛው የቤቱ ጣራ የተሠራበትን የሕንፃ ዕቃ ዓይነት በመጠየቅና በተሰጠው መልስ ከሚከተሉት የኮድ ዝርዝሮች ውስጥ በትክክለኛው ኮድ ከብ በማድረግ ይሸው ኮድ በካርድ ኮለም 34 ውስጥ ይሞላል፡፡ ከተዘረዘረው ኮድ ውጭ ካጋጠመ ሌላ በሚለው አቅጣጫ የቤቱ ጣራ የተሠራበት የዕቃ ዓይነት ተመዝግቦ በካርድ ኮለም 34 ውስጥ ኮድ 7 ይሞላል፡፡

1 = ቆርቆሮ
2 = ኮንክሪት/ሲሚንቶ
3 = እንጨትና ጭቃ
4 = ሣር
5 = ሸንበቆ
6 = አስቤስቶስ
7 = ሌላ /ይገለጽ______

ዓምድ 47 የቤቱ ወለል አበዛኛው የተሠራው ከምንድን ነው ?

አበዛኛው የቤቱ ወለል የተሠራበትን የሕንፃ ዕቃ ዓይነት በመጠየቅ ለተሰጠው መልስ ከሚከተሉት የኮድ ዝርዝር ውስጥ በትክከልኛው ኮድ ከብ በማድረግ ይሸው ኮድ በካርድ ኮለም 35 ውስጥ ይሞላል፡፡ ከተዘረዘሩት ኮዶች ውጭ ካጋጠመ ሌላ በሚለው አቅጣጫ የቤቱ ወለል የተሠራበት የዕቃ ዓይነት ይመዘገብና በካርድ ኮለም 35 ውስጥ ኮድ 8 ይሞላል፡፡

0 = አፈር
1 = ሣንቃ
2 = ሲሚንቶ/ሊሾ/
3 = ፕላስቲክ ንጣፍ
4 = ስሚንቶ ሸክላ ንጣፍ
5 = ማርሞ ንጣፍ
6 = ድንጋይ
7 = ሸንበቆ ወይም ቀርቅሃ
8 = ሌላ ይገለጽ______

ዓምድ 48 አበዛኛው የቤቱ ክፍል ኮርኒስ አለው ወይ ?

ኮርኒስ፡- ከቤቱ ጣራ በታች ትንሽ ዝቅ ብሎ የሚገኘ የቤቱ ወይም የክፍሉ የውስጥ ከፃን ኮርኒስ ይባላል፡፡ ኮርኒስ ከቤቱ ገጽግና ጣራውን ከደገፈው እን ጨት፣ ብረት፣.... ወዘተ የተያያዘ ሆኖ በጨርቅ፣ በባንቃ፣ በኮንፔንሳቶ፣ በች ፕ በርድ፣ በሲሚንቶ.... ወዘተ ሊሠራ ይችላል፡፡

አበዛኛው የቤቱ ክፍል ኮርኒስ አለው ወይ ብሎ በመጠየቅ ለተሰጠው መልስ ቀጥሎ ከረዘረዘረው በትክክለኛው ኮድ ዙሪያ ከብ በማድረግ በካርድ ኮለም 36 ውስጥ

መጸዳጃ ቤት እንደሌለው ይቆጠራል።

1 = መጸዳጃ የለውም　　4 = የጉድጓድ መጸዳጃ የግል
2 = በውኃ የሚወርድ መጸዳጃ የግል　　5 = የጉድጓድ መጸዳጃ ለጋራ
3 = በውኃ የሚወርድ መጸዳጃ ለጋራ

ዓምድ 58 ቤቱ ምን ዓይነት መብራት አለው ?

ቤቱ ምን ዓይነት መብራት እንዳለው በመጠየቅ ከዚህ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ኮዶች ውስጥ በትክክለኛው ክብ በማድረግ ይሸው ኮድ በዓምድ 58 በካርድ ኮለም 50 ውስጥ ይሞላል።

1 = ኤሌክትሪክ ቆጣሪው የግል
2 = ኤሌክትሪክ ቆጣሪው የጋራ
3 = ማሾ
4 = ፋኖስ
5 = ኩራዝ
6 = ሌላ /ይገለጽ/ ________

ዓምድ 59 እዚህ ቤት ሬዲዮ አለ ?

የቤቱ ነዋሪዎች ሬዲዮ እንዳላቸው በመጠየቅ ቀጥሎ ከተሰጡት ኮዶች በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይሸው ኮድ በዓምድ 59 በካርድ ኮለም 51 ውስጥ ይሞላል።

1 = አለ /ሬዲዮ አላቸው/
2 = የለም /ሬዲዮ የላቸውም/

ዓምድ 60 እዚህ ቤት ቴሌፎን አለ ?

በቤቱ ቴሌፎን እንዳለ በመጠየቅ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ኮዶች በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይሸው ኮድ በዓምድ 60 በካርድ ኮለም 52 ውስጥ ይሞላል።

1 = አለ /ቴሌፎን አላቸው/
2 = የለም /ቴሌፎን የላቸውም/

ዓምድ 61 እዚህ ቤት ቴሌቪዥን አለ ?

ቤቱ ቴሌቪዥን እንዳለው በመጠየቅ ቀጥሎ ከተሰጡት ኮዶች በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይሸው ኮድ በዓምድ 61 በካርድ ኮለም 53 ውስጥ ይሞላል።

